# እውነት መንፈሳዊ ጋዜጣ



# በውስጥ ገጾች

## ❖ ዕርሰ አንቀጽ፤

እኛ የዓለም ብርሃን ነንና ብርሃኑን ኢየሱስን በእያንዳንዳችን ሕይወት እናብራ።

## ❖ ምስክርነት፤

እጢው ሲመረመር ካንሰር ሆኖ በመገኘቱ ጡቴን ለመቆረጥ ……

## ❖ ዝም በሉ

የሚገርማችሁ የኤልሳ ጥያቄ ኤልያስን አስደነገጠው እሳት ከሰማይ ይውረድ ሲል ሰማይ ይዘጋ ሰማይ ይከፈት ሲል በሙሉ ልቡ እንዳልተናገረ እንደምንምትንፋሹንዋጥ አድርጎ……….

## ❖ የግጥም መድብል፤

**ሟች ስም ወጣለት**

ገዳይ ተሸነፈ
ቆሞ ተሸነፈ
ብርታቱ ረገፈ፤

***ተናገር ዝም አትበል***

*ጩኸቱም በርክቷል ካቀበቱ ወዲያ*

*የድረሱልኝ ድምፅ የሰዎች ጫጫታ*

*ማን ይሆን ጣልቃ ገብቶ ችግር የሚፈታ*

*የታመነ ባሪያ የሚኖር ለጌታ፤*

በቦስተን የምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ የምታምን የክርስቶስ ኢየሱስን የማዳን ወንጌል ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ የምታሰራጭ ቤ/ክ ነች። ይህም ጋዜጣ ወንጌልን ከምታሰራጭባቸው መንገዶች አንዱ ሲሆን በቤ/ክ የሥነ-ጽሁፍ አገልግሎት አባላት እየተዘጋጀ በየሁለት ወር አንድ ጊዜ ይቀርባል።

የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ
ፖስተር ምሕረቱ ሌጂቦ
Email Meheretu2614@Yahoo.com
Telephone 617-792-5764

ዋና አዘጋጅ……………… ሄኖክ ተሾመ
ምክትል አዘጋጅ……..ሐብታሙ አስረስ
የውብዳር ፍሰሐ
ኮምፒዩተር ጽሑፍ…..ትርሲት ጥላሁን
የፊት ገጽ ዲዛይነር…የዝግጅት ክፍሉ

ለቀጣዩ እትም ይረዳ ዘንድ የእናንተ ተሳትፎ ወሳኝ ሚና ስላለው በሚቀጥለው አድራሻ ያላችሁን አስተያየትና ጥያቄ ላኩልን። አድራሻ ……………….

Ethiopian Evangelical Church in Boston
88 Tremont Street
Boston, MA 02108
Tel. 617-816-8827



# ርዕሰ አንቀጽ

## በያለንበት እናብራ

አሁን ያለንበት ዘመን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ለጌታ መምጣት እጅግ የተቃረብንበት ዘመን ነው፤ ጌታ ኢየሱስ የኛን የሥጋ አካል ለብሶ በምድር በነበረበት ዘመን እንኳን የመጨረሻው ዘመን ተብሏል አሁን ያለበት ጊዜው የመጨረሻው ዘመን ብቻ ሳይሆን የመጨረሻው ሰዓት ቢባል ማጋነን አይሆንም።

እንግዲህ ጌታ ይመጣል ብለን የምናጠብቅ በክቡር ደም የተዋጀን የሰማይ ሃገር ዜጎች የሆንን ሁላችን በመምጣቱ ቀን የማናፍር እንድንሆን ዛሬ ቀን እያለ ልንኖር የተጠራንበት ሕይወት እርሱም በክርስቶስ እግዚአብሔርን እየመሰልን መኖር ነው።

በክርስቶስ እግዚአብሔርን እየመሰልን መኖራችን የመዳናችን ምልክትና የምናመልከው አምላክ ማን እንደሆነና ለምናመልከው አምላክ ያለንን ፍቅርና አክብሮት ያመለክታል።

የጨለማው ሥራ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ እይሏል እንግዲህ እኛ የዓለም ብርሃን ነንና ብርሃኑን ኢየሱስን በእያንዳንዳችን ህይወት እናብር የብርሃኑ መጠን ተዳምቆ የሚታየው እኛ ክርስቶስን በመምሰል ባደግን መጠን ነው።

በዓለም ካለው የጨለማ ኃይልና አሠራር በእኛ ያለው የብርሃን ኃይል ብርቱ ነውና ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅና በመምሰል እየኖርን እናብራ በድቅድቅ ጨለማ ያሉ ወደሚደነቀው ብርሃን ይመጡ ዘንድ በያለንበት እናብራ እናብራ !!

የቤተ\ክርስቲያኒቷ መልዕክት



## ምስክርነት

# የሞት ፍርሃት ...

ሮማን ትባላለች በቶሮንቶ ያለችው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን አባል ናት፤ ሮማን በሳቋ ትታወቃለች ሁል ጊዜም ፈገግታ ከፊቷ ላይ አይታጣም ጌታ ያደረገውን ልትመሰክሪ ፈቃደኛ ነሽ ወይ ? ብዬ ስጠይቃት በደስታ ፈቃደኝነቷን ገልጸችልኝና እኔ ያቀረብኩላትን ጥያቄዎች በሙሉ ካዳመጠች በኋላ በራሷ ቋንቋ እንደሚከተለው ተርካልኛለች።

እግዚአብሔር መልካም ነው በመከራም ቀን መሸሸጊያ ነው፤ከእግዚአብሔር ምሕረትና ቸርነት የተነሣ እኔም እግዚአብሔር በሕይወቴ ያደረገውን ለመመስከር ይህን እድል ስላገኘሁ በቅድሚያ እግዚአብሔርን እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።



ወ/ሮ ሮማን

ተወልጄ ያደግሁት በአዲስ አበባ ከተማ ሲሆን ራሴን ክርስቲያን አድርጌ የምቆጥር ሰው ነበርኩ፤ ነገር ግን ለሃይማኖቱም ሆነ ለእግዚአብሔር ግድ የሚለኝ ሰው አልነበርኩም፤ ይህ በዚህ እንዳለ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1990 ዓ.ም በመጨረሻ ላይ እኔና ውድ ባለቤቴ ዳኒ በተለያዩ ምክንያቶች የተወለድንበትን አገር ለቀን ወደ ግሪክ አገር መጣን ያም ሥፍራ ጌታ ለኛ አስቀድሞ ያዘጋጀልን በመንፈስ ዳግም ልደት የምናገኝበት ሥፍራ ሆነልን በ1991 ዓ.ም ጌታን እንደ ግል አዳኛችን አድርገን ተቀበልን፤ የእግዚአብሔር መልካምነትና ፍቅር በሕይወታችን እንደ ወንዝ ፈሰሰ ኑሮ ከጌታ ጋር እንዴት ያስደስታል እንዴትስ ያስደንቃል ጌታን ከተቀበልንበት ጊዜ ጀምሮ ታላቅ ለውጥ በሕይወታችን ውስጥ እየተከሰተ መምጣት ጀመረ፤ አስተሳሰባችን ተለወጠ የኑሮ ትርጉም ምን እንደሆነ እግዚአብሔር አስተማረን፤ በምንም ሁኔታ ውስጥ ብናልፍ በከፍታም ሆነ በዝቅታ እግዚአብሔር መኖሪያችን እና ትምክህታችን ሆኖ አሳየን በዚያም ስፍራ ጌታ በሴት ልጅ ባረከን፤ በመጨረሻም ወደ ካናዳ ለመምጣት በሚያስፈልገን በእያንዳንዱ ነገር ውስጥ ጣልቃ እየገባ ወደ ካናዳ ምድር እንድንመጣ መልካም ፈቃዱ ሆነ በሁለተኛ ሴት ልጅም ተባረክን ሁሉ በተሟላበት ሁኔታ በሰላም ደስ እያለን ስንኖር ግን አንድ ቀን ሕይወታችንን የሚያናውጥ ችግር ተከሰተ፤ ይህ ከመሆኑ በፊት ግን እግዚአብሔር ከበጎ ፈቃዱና ከምሕረቱ የተነሣ በሕይወቴ ውስጥ ሊመጣና ወደ ፊት ሊሆን ያለውን ነገር በሕልም አሳየኝ ሕልሙም እኔን ብቻ ሳይሆን አንዷት በጌታ ያለች እህትንም የሚመለከት ነበር በዚያን ጊዜም ሕልሙን በአእምሮዬ ለመተርጎም ሞከርኩ ሕልምን መተርጎም የሚቻለው እርሱ ራሱ እግዚአብሔር የሕልሙን ትርጉም ሲሰጥ እንደሆነ ተገንዘብኩና ያየሁትን ሕልም ለዚያች እህት ነገርኳት ትርጉሙ ባይገባኝም እንኳ እግዚአብሔር ይህን ሕልም ሲያሳየኝ ምክንያት አለው አልኳት በመቀጠልም በሕይወትሽ ውስጥ በምን ሁኔታ ላይ ነው ያለሽው ብዬ ጠየቅኳት እሷም በጤናዋ ከፍተኛ ምርመራ በማድረግ ላይ እንዳለች እና እንድጸልይላትም ጠየቀችኝ እኔም የእግዚአብሔር ነገር አስገርሞኝ አይዞሽ ጌታ ነገርሽን አይቷል እርሱ በረዳኝ መጠን እጸልያለሁ ነገር ግን እኔም በሕልሙ ውስጥ ስላለሁበት ለእኔም ደግሞ ጸልይልኝ ብዬአት ተለያየን።

ይህ በእንዲህ እያለ ለሁለተኛ ጊዜ ከዚያች እህት ጋር ሆኜ ሕልም አየሁኝ ሕልሙም ግራ ጡቴ ላይ እጇን ጭኜ እያሳየኋት ይኸውልሽ እኔም እኮ ጡቴን አመመኝ ለእኔም ጸልይልኝ ብዬ ስላት እሷም ከሰማችኝ በኋላ እኔም ያኔ ምርመራ ላይ ነኝ ያልኩሽ እኮ ጡቴን አሞኝ ነው ብላ ስትነግረኝ ከሕልሜ ባነንኩ አሁን ነገሩ ከምንጊዜውም በላይ ግልጽ ስለሆነልኝ ያችን እህት ቤተክርስቲያን አገኘኋትና ድጋሚ ያየሁትን ሕልም ስነግራት እውነት እንደሆነና እርሷም ጡቷን እንደታመመች ስትነግረኝ በጣም ደነገጥኩ በጣምም መገረም ሞላኝ አሁንም በድጋሚ አይዞሽ እግዚአብሔር ነገሮቻችንን እይቷልና ምንም አንሆንም ነገር ግን እርስ በእርሳችን እንሸካከም ተባብለን ተለያየን።

ብዙም ጊዜ ሳይቆይ ከወር በኋላ በሕልም እንዳየሁት በግራ ጡቴ ላይ ሕመም ተሰማኝ እጄንም ጭኜ ስፈትሽ ትንሽ እጢ በጡቴ ውስጥ አገኘሁ ወዲያውኑም ወደ ሐኪም ቤት በመሄድ መደረግ የሚገባውን ምርመራ ሁሉ አደረግሁኝ ምርመራውን በማድረግ ላይ እያለሁ ግን በሐሳቤ ውስጥ የሚመላለሱ ብዙ ጥያቄዎች ነበሩ ለምን ጌታ በቅድሚያ ይህ ነገር በሕይወቴ ውስጥ እንዲያልፍ ነገረኝ?

ቀጣዩ ወደ ገጽ 6....ዞሯል

# ዝም በሉ !

ዝም በሉ ይህ ቃል በዛ ያሉ ዓመታቶች የኋልዮሽ ተጉዤ ከብሉይ ኪዳን አንድ የእምነት ጀግና በአእምሮዬ አብሰለሰል ዘንድ አሳብ ይጭርብኛል ወይ ጉድ እንዴት ያለ ጠንካራ ሰው ነው እላለሁ ቃሉን ሳስበው ደግሞም ደፋር የማያወላዳ ቆራጥ ጽኑ የዓላማ ሰው ሁሌ ከፊት ያለውን ግብ ብቻ የሚያይ ጀግና ይገርማችኋል ይህን ሰው ሳስበው እኔም እራሴ ይሸንጠኛል ምን አለ እኔም ለአምላኬ እንዲህ ብሆንለት እላለው ዋ.... እንዴት ያለ ኩሩ የእግዚአብሔር ሰው ነው ምንም ሳያይ ቤቱን ቄዬውን አባቱን እና እናቱን ኑሮውን ሁሉን ትቶ በቆራጥነት ለእግዚአብሔር ሥራ የወጣ ለአፍታ እንኳን ወደ ኋላ ለመመለስ ሳያስብ የተጓዘ ብርቱ ይደንቀኛል ወይ ጉድ ስንት ብርቱ ሰዎች ከፊት አሉልን እንድል ያደርገኛል መቼስ ማንነቱን ሳይነግረን ምነውሳ ይሄ ሁሉ ተጓዘ እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ ከኤልያስ ለጥቆ የተነሳ ፊት አውራሪ ነብይ ነው ኤልሳእ ይህ ንግግሩ ብዙ ሰዎችን ያስደንቃል ወገኖቼ ዛሬም በዚህ ዘመን ያላችሁ እውነተኛ ባለ ራእዮች ሰማያዊ ጥሪና ተልእኮ ያላችሁ ማቄን ጨርቄን ሳትሉ ለሰማችሁት እውነት ለተቀበላችሁት መለኮታዊ አደራ እራሳችሁን ለሰዋችሁ በሙሉ ዛሬ አንድ ሚስጥር ሹክ ልላችሁ አሰብኩ ዝም በሉ፤ ከዓላማችሁ ከራእያችሁ ጌታ ካሳያችሁ ግብ ከተቀበላችሁት መለኮታዊ ጥሪ ወደ ኋላ ሲመልሷችሁ ያሉትን ሰዎች ቢሆኑ ሁኔታዎች ቢሆኑ ምንም ምንም ቢሆኑ ዝም በሉ በሏቸው እናንተ ግን ጉዞአችሁን ቀጥሉ።

መጽሐፍ ቅዱስን ስታነቡ 1ነገሥ ላይ እግዚአብሔር ኤልያስን በአንተ ፈንታ በእስራኤል ላይ ነብይ ይሆን ዘንድ የሳፋጥን ልጅ ኤልሳእን ቀባው ሲለው ኤልያስም ኤልሳእን በአሥራ ሁለት ጥማድ በሬ ሲያርስ እርሱም ከአሥራሁለተኛው ጋር ሆኖ አግኝቶት መጎናጸፊያውን እንደጣለበት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኤልሳእ እንደ ጥንቱ መሆን እንዳልቻለ ማንነቱ አስተሳሰቡ ዓላማው ሁለንተናው እንደተቀየረና ከዚያም የተነሳ አባቱን እና እናቱን ተሰናብቼ ልምጣ እንዳለው ኤልያስም መልሶ እኔ ምን አደረኩህ ሲለው ተጽፎ እናገኛለን 1ኛ ነገሥ 19፡11-20

ይህንን ክፍል ልብ ብላችሁ ስታነቡት አንድ አስገራሚ ነገር ገና ከጅምሩ ታገኛላችሁ ያም ኤልያስ የሰውየውን መላ ማንነቱን የቀየረ ሥራ ሰርቶ ምን አደረኩህ ሲለው ምን ማለቱ ነው ምን አደረኩህ ይለዋል እንዴ? እንዴት ያለ ነገር ነው ልብ በሉ የኤልሳእ የዓላማ ጽናት የተጀመረው እዚህ ጋር ነው ፈቃዱን ሳይጠይቀው መጎናጸፊያ ጥሎበት ልቡን ሰርቆት ኑሮውን ቤቱን ንብረቱን እናቱን እና አባቱን አስጥሎት የሚያስወጣ ዓላማ ጭርበት ምን አደረኩህ ይለዋል አይ ኤልያስ ንግግሩ አይደንቃችሁ ምን አደረኩህ በዚህ ሁሉ ደግሞ የኤልሳእ ውሳኔ ይበልጥ ያስደንቀኛል ምን አደረኩህ ቢለውም ግራ አልገባውም መብቱን ጥሶ ልቤን ሰርቀኸው ብሎ ለጠብ አልተነሳም ምክንያቱም በውስጡ መለኮታዊ ጥሪ ገብቷል አንድ ነገር ብቻ ለመነው እናቴንና እና አባቴን ተሰናብቼ ልምጣ ፈቀደለት በሬዎቹን አረደ ሞፈር ቀንበሩን ሰባበረ ሥጋቸውንም ቀቅሎ ሁሉን አበላ እናቱን እና አባቱን ተሰናብቶ ወደ ኋላ ላይመለስ ከሞቀ ቤቱ ከሃብቱ ከነበረው የወደፊት ዓላማ ፈጽሞ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ቀሪ ዘመኑን ሊመራ ማደሪያ ሆነ አድራሻ የሌለውን ኤልያስን ተከትሎ ሄደ 1ኛ ነገሥ 10፡21፤

ነገር ግን ከጥቂት የአገልግሎት ጊዜ በኋላ በፍጹም ያልጠበቀው አስደንጋጭ ነገር ገጠመው ያዋጣኛል ዓላማዬ ነው ብሎ ተከትሎት የሄደው ኤልያስ ከእርሱ ሊለይ እንደሆነ አወቀ ምን ያድርግ ወደ ኋላ አይመለስ ነገር ሁሉን ጥሎ ዳግም ላያያቸው አርዶ ሰባብሮ ነው የወጣው በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ ጌልጌላ ላይ ሳሉ እንዲህ አለው ኤልሳእ እግዚአብሔር ወደ ቤቴል ልኮኛል አንተ በዚህ ቆየኝ ከዚህ በፊት በነበራቸው የአገልግሎት ጊዜአቶች አንድም ቀን እንዲህ ብሎት አያውቅም የገባበት የወጣበት የሄደበት ሁሉ ይዞት ይጓዝ ነበር ዛሬ ግን ያልተለመደ ትእዛዝ ሆነበት ቢሆንም ቆፍጠን ብሎ ህያው እግዚአብሔርን በህያው ነፍስህ እምላለው አልለይህም አለው ኤልያስ ሳይደንቀው አልቀረም ምክንያቱም እስከዛች ቀን ድረስ ኤልሳእን ሲያውቀው ታዛዥ ያለውን ሁሉ የሚያደርግ ትሁት ሰው ነበር የዚያን ቀን ግን አንገቱን በካራ ይህችን ትእዛዝ አልቀበልም አለው ሁሉን ትቼ ታዋጣኛለህ ብዬ የተከተልኩህ አውላላ ሜዳ ላይ እንድትጥለኝ አይደለም እኔ እንደው የት እንደምትሄድ ገብቶኛል ሳይለው አይቀርም አንደበቱ ባይናገርም ኤልያስ ምንም ማድረግ ስላልቻለ ተያይዘው ጉዞ ጀመሩ ቤቴል እንደደረሱ በድጋሚ ኤልሳእ አለው አቤት ጌታዬ ይኸውልህ እግዚአብሔር ወደ ኢያሪኮ ልኮኛል አንተ በዚህ ቆየኝ ቢለው አ...ኼ...ኼ ኤልያስ ህያው እግዚአብሔርን በህያው ነፍስህ እምላለሁ አልለይህም እኔ እንደው ነቅቼብሃለሁ አትድከም አንላቀቅም እያለ የተጣበቀ መጣበት ይባስ አከረረው ኢያሪኮ እንደደረሱ በድጋሚ ኤልሳእ አለው አቤት ጌታዬ እግዚአብሔር ወደ ዮርዳኖስ ልኮኛልና አንተ በዚህ ጠብቀኝ አለው እዚህ ጋ እኔ በጣም የገረመኝ ነገር ቢኖር ኤልያስ እኮ ለምን እዚህ ጠብቀኝ እንደሚለው ኤልሳ ያውቃል ቢሆንም አቤት ትእግስቱ ዝም አለ አይ እኛ ብንሆን ስንቱን በዘከዘክነው ነበር አንተ ኑሮዬን እናቴን እና አባቴን ሁሉን ትቼ ተከትዬህ ጉድ ልትሰራኝ እኔስ ደህና ሰው ትመስለኝ ነበር ለካስ እንዲህ አይነት ጨካኝ ነህ ልትነጠቅ መሆኑን ያላወኩ መሰለህ እያልን ልክ ልኩን እንነግረው ነበር ።

ቀጣዩ ወደ ገጽ 7 ዞሯል

*ከገጽ 4 የዞረ ........የሞት......*

*ይህን ከአሳየኝ ደግሞ እግዚአብሔር በሕይወቴ ውስጥ ለምን ተአምር አያደርግም? ለምንስ እጢው አይሚሽሽም? እል ነበር። ጌታ እጢውን ያሚሽሽዋል ምንም ዓይነት ሕክምና አያስፈልገኝም እርሱ ያለ ሐኪም እርዳታ ይፈውሰኛል የሚል ፍላጎትና ሃሳብ በውስጤ ሞልቶ ነበር በዚህን ጊዜ በግልም ሆነ በሕብረት በአቅራቢያዬ ካሉ የጌታ ልጆች ጋር ሆነን መጸለይ ጀመርን፤ ፍላጎታችንም ሆነ እመነታችን ጌታ እጢውን አሚሽሾት ማየት ነበር በነገራችን ላይ ያዊ በሕልሜ ያየኋት ልጅ የሕክምናዋን ውጤት ማለት ምንም ዓይነት በሽታ እንደሌለባት ተነግሯት ነፃ መሆኗን የምሥራች ነገረችኝ በዚህም ጊዜ እኔም እንደርሷ ነፃ እሆናለሁ ብዬ አሰብኩ ይህ በእንዲህ እንዳለ የቀጠሮዬ ጊዜ ደርሶ ......!ሌላ በሙያው የሰለጠነ ሐኪም ለማየት ሔድኩኝ እርሱም ቀዶ ጥገና እንደሚያስፈልገኝና ሌላ ምርመራ እንደሚያደርግ ነግሮኝ በቀጠሮ ተለያየን በዚያን ጊዜ በቅርብ ያለች ጓደኛዬ በአንድ ሐኪም አስተያየት ብቻ ሄደሽ ቀዶ ጥገና አታደርጊም የሌላ ሐኪም ሁለተኛ አሳብ ያስፈልግሻል ብላ ወደ እርሷ ሐኪም ጋር ቀጠሮ ይዛ ወሰደችኝ ወደ ክሊኒኩ ስንሄድ የሐኪሙ ቢሮ ተዘግቶ አገኘን በጣም ግራ ተጋብተን እያለ ዘወር ስል በዚያ ሕንፃ ላይ ብዙ የሐኪም ቢሮዎች እንዳሉ ተመለከትኩ አንድ ሐሳብ በውስጤ መጣ ለጓደኛዬ አሁን አንቺ ሐኪም ጋ የመጣሁት ለሁለተኛ አሳብ ነው :*

*ስለዚህ ከእነዚህ አንዱ ሐኪም ዘንድ ገብቼ አዲስ በሽተኛ ከተቀበሉ የሚሉትን እሰማለሁ እንጂ እዚህ ድረስ መጥቼ እንዲሁ አልመለስም እልኳትና ዘው ብዬ በአእምሮዬ ወደ መረጥኩት ክሊኒክ ገብቼ ጸሐፊዋን ሐኪም ማየት እችል እንደሆነ ጠየቅኋት፤ እሷም ትንሽ ጊዜ እንደሚያስጠብቀኝ ነገረችኝና ተራዬ ሲደርስ ገባሁ ሐኪሙም በእድሜ የጠኑ ማለትም በጡረታ ውስጥ ያሉ ነገር ግን የራሳቸው ክሊኒክ ያላቸው ነበሩ።*

*ባየኋቸው ጊዜ አይ እኚህ ምንም የሚያውቁ አይመስሉም ምን ቸገረኝ ለሁለተኛ አሳብ ስለሆነ የመጣሁት ያሉትን ይበሉ በሚል ስሜት ወደ ውስጥ ገባሁ እሳቸውም ለምን እንደመጣሁ ከጠየቁኝ በኋላ ወደ ሌላ ምርመራ ክፍል ውስጥ እንድገባ ነገሩኝ በዚያች ትንሽ የምርመራ ክፍል ስገባ በመጀመሪያ ዓይኔ ያረፈው አንድ የመጽሐፍ መደርደሪያ ላይ ነበር።*

*በመደርደሪያው ላይ በተለያዩ ቋንቋ የተተረጎሙ መጽሐፍ ቅዱሶችን የተለያዩ የመንፈሳዊ መጽሐፍትን Daily bread booklet እና የመሳሰሉትን ተመለከትኩኝ ነገሩ በጣም ገርሞኝ ልብሴን ማውለቅ ትቼ መጽሐፎቹን ለማየት ሙከራ በማድረግ ላይ ሳለሁ ሐኪሙ በሩን አንኳኩተው ገቡ፤ ፈጥኜ ወደ አልጋው ላይ ሄጄ ተቀመጥኩና ወዲያው "Are you born again?" አልኳቸው እሳቸውም ፈገግ ብለው "indeed I am Indeed I am" ብለው ሲመልሱልኝ እኔም በጌታ ነኝ ብዬ አልኳቸው ከየትኛው ቤተክርስቲያን ነው የመጣሽው ማን ወደ እኔ ላከሽ ብለው ሲጠይቁኛ እኔም እንዴት ወደ እሳቸው ጋ እንደመጣሁ የሆነውን ሁኔታ ስነግራቸው በእግዚአብሔር አሠራር በጣም ተደነቁና ለአንድ ለአሥራ ደቂቃዎች ስለ እግዚአብአሔር አባትነትና እንዴት እንደሚጠነቀቅልኝ የሚያሳይ ትንሽ ቃል ካካፈሉኝ በኋላ ደግሞ ወደ ምርመራ ገብተው ስለ በሽታው አስረድተውኝ በሙያቸው Surgeon መሆናቸውን ነግረውኝ ወደፊት ምን ዓይነት ምርመራ ማድረግ እንዳለብኝ አስረድተውኝ ተሰነባበትን።*

*ከዚያም መደረግ የሚገባውን ምርመራ አደረግሁኝ ጌታ የራሱ የሆነ ሐኪም ሰጥቶኝ ማየት ለኔ እንደ ተአምር ነበር፤ በተጨማሪ ደግሞ አሁን ይህ እጢ ይሚሽሻል ከውስጤ እንድምናምን ይጠፋል የሚል ታላቅ ተስፋ አደረብኝ ነገር ግን እጢው ከእለት እለት እያደገ እብጠቱ እየጨመረ መምጣቱን ያዩት ሐኪም ሆስፒታል ቀጠሮ እንዲያዝልኝ አድርገው በአፋጣኝ ቀዶ ጥገና አደረጉልኝ እጢው ሲመረመር ካንሰር ሆነ ስለተገኘ ጡቴን ለመቆረጥ በቃሁ።*

*የእግዚአብሔር ሰላም ድንቅ ነው ካንሰር ተብሎ ሲነገረኝ ምንም ዓይነት ፍርሃት በውስጤ አላደረም ነበር ለራሴም እስከሚደነቀኝ ድረስ ጌታ ውስጤን በምስጋና ሞልቶት ነበር የበሽታ የመጨረሻ ደረጃው ሞት ቢሆንም እንኳ አማኝ ከሆንን ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚል የቅዱሳን ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው በዚህ በሽታ ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት ብለይ ከጌታ ጋር ፊት ለፊት የምንገናኝበትና በዚያኛው ዓለም የምኖረው ኑሮ መጀመሪያ እንደሚሆን ስለማውቅና እንዲሁም የዘለአለም ሕይወት ምን እንደሆነ ስለገባኝ የሞት ፍርሃት በምንም ዓይነት ወደ ውስጤ አልገባም ነበር።*

*ከቀዶ ጥገና በኋላ ደግሞ ካንሰሩ ከተቆረጠው ጡቴ ወደ ሌሎች የሰውነት ክፍሎች በውስጤ አለመሰራጨቱን ለማረጋገጥ ስድስት ሳምንት የሚፈጅ ምርመራ እንዳለ ተነገረኝ ውጤቱን በመጠባበቅ ላይ እያለሁ የኔ ጌታ ኢየሱስ እንደገና ሕልም አሳየኝ፤ ቦታው ኢትዮጵያ ውስጥ ይመስለኛል ወቅቱ በጋ ስለሆነ የለበስኩት ልብስ የበጋ ስስ ቀሚስ ነው ከአንዲት የድሮ ጓደኛዬ ጋ ቆሜ ሳለሁ ጀርባዬ ውስጥ የሆነ ነገር ይሄድብኛል በዚህን ጊዜ ጓደኛዬ ጀርባዬ ውስጥ አንድ ነገር ይሄዳል እባክሽ ምንድነው እይልኝ ብዬ ስጠይቃት እጇን በቀሚሴ ውስጥ አስገብታ እባብ ነው እባብ ነው ብላ ጅራቱን ይዛ መዛ አውጥታ ፊት ለፊቴ ላይ ስትከስክሰው ጭንቅላቱ ሲፈረካከስ ከእንቅልፌ ባነንኩ፤ የምርመራው ውጤትም መልካም ዜና ይዞ እንደሚመጣ አመንኩ፤ እንደ ሰው ግን ውጤቱን መጠበቁ አልቀረም ጊዜው ደርሶ ውጤቱ ሲመጣ ጌታ እንዳሳየኝ ምንም ዓይነት የካንሰር መሰራጨት እንደሌለ ተነገረኝ፤ ኢየሱስ ጌታ ነው፤ ከዚያ በኋላ ይህም እንኳ ቢሆን ማለትም ካንሰር ባይሰራጭም እጢው ካንሰር ሆኖ ስለተገኘና ሕክምናውን መቀጠል*

እንዳለብኝ ስለተነገረኝ ለአንዱ ዓመት ያሕል chemotherapy and radiation ሕክምና ወስጄ አሁን ከካንሰር ፍጹም ነፃ ሆኛለሁ፤ በዚህ ሁሉ ሳልፍ ግን ብቻዬን አልነበርኩም የቅዱሳን ፀሎት በሥራዋ እጅግ ሃይልን ታደርጋለች ተብሎ እንደተጻፈ በእውነት የእግዚአብሔር ልጆች እንደ አንድ ሰው ሆነው በእግዚአብሔር ፊት በብዙ እንባ በጸሎትና በምልጃ በጌታ ፊት ያቀርቡኝ ነበር፤ እነሆ እኔም መልስ ሆኜ ይችን ልተርክ በቅቻለሁ።

በጸሎት በአካል መጥቶ በመጠየቅና በሚያስፈልገኝ ሁሉ ያጽናናችሁኝ ሸክሜን ሁሉ የተሸከማችሁ በቶሮንቶ ያለችው ቤተክርስቲያንና በካዳና የምትገኙ ቅዱሳን ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

ውድ ወገኖቼ እኛ እንደ ማንም አይደለንም በዋጋ የተገዛን በከበረው ደሙ የተዋጀን እንደ ዓይኑ ብሌን የሚጠብቀን በእጆቹ መዳፍ የቀረጸን ሰዎች ስለሆንን በምንም ውስጥ ብናልፍ እግዚአብሔር እርሱ እንደ ቃሉ ከእኛ ጋር እንዳለ ለአፍታ እንኳን እንዳንረሳ እለት እለት ኃይል እና እውቀት እንዲሞላን መጸለይ ይገባናል፤ ኢየሱስ ለዘለአለም ጌታ ነው አሜን::

*(በቶሮንቶ በምትግኘው በኢ.ወ.ቤተ-ክርስቲያን አማካኝነት በ2008 ታትሞ ከወጣው ከአማኑኤል መንፈሳዊ መጽሔት ከቁ.1 የተወሰደ)*

ከገጽ 5 የዞረ....ዝም....

ሌላው የደነቀኛ በቤቴል በኢያሪኮ ያሉ የነብያት ልጆች የኤልያስ እዚህ ቆየኝ የሚለው ጭቅጭቅ አይበቃውም ብለው በኤልሳእ ላይ ሌላ የእግር እሳት መሆናቸው ነው ጌታህን ዛሬ እግዚአብሔር ከራስህ ላይ ሊወስደው ነው ምን ይውጥሃል የምትሆነውን እናያለን እያሉ ልቡን የሚያቀልጥ ነገር ይናገሩት ጀመር አይ ኤልሳእ እሱ እንደው ምን ገዶት የዐላማ ሰው አይደል የኤልያስን አፍ እየዘጋ በመጣበት ብርታቱ የነብያትንም ልጆች አፍ ያዘጋ ጀመር ዝም በሉ አውቄአለሁ እያለ እንዴት ደስ ያሰኛል የዓላማ ጽናቱ በአንድ በኩል ኤልያስ በሌላ በኩል የነብያት ልጆች እናቱን እና አባቱን ኑሮውን ሁሉን ትቶ የወጣለት ዓላማ ሊያስጥሉት ተረባረቡበት።

ኤልሳእ የእምነት ጀግና ጽኑ ሰው ነው ነብዩ ምንም የእፉ ቃል መሬት ጠብ የማይል እንደሆነ ቢያውቅም እዚህ ጋ ግን ቀልድ የለም አለው ህያው እግዚአብሔርን በህያው ነፍስህ እምላለሁ አልለይህም።

ሌላው በዚህ ክፍል እጅግ ያስገረሙኝ የነብያት ልጆች የሚባሉት ናቸው በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ የነብያት ልጆች የሚባሉት እነማን ናቸው ቢባል በታላላቅ ነብያት ሥር የሚያድጉ ወደ ፊት በእነርሱ እግር የሚተኩ ሲሆኑ በሁለቱም ስፍራ ለኤልሳእ ያመጡለት መልእክት ትክክል ነው ታዲያ ምን ያስገርምሃል ብትሉኝ የኤልሳእን ራእይ (ዓላማ) ለመደገፍ ሳይሆን ልቡን ለማሳዘን መሆኑ ነው እንዲያውም ነገሩን ልብ ብላችሁ ብትመለከቱት ደግሞ ከኤልሳእ ጋር እልህ ያለባቸው ይመስላል ይሄ ዛሬ ከኤልያስ ኋላ ኋላ የሚከተል እሱ ቢወሰድ( ቢነጠቅ) የእርሱን ቦታ ለመተካት ሳይሆን አይቀርም ስለዚህ ከአሁኑ ቅስሙን መስበር ነው የሚሉ ይመስላሉ ዛሬ እግዚአብሔር ጌታህን ከራስህ ላይ ሊወስደው ነው ነብይ ነኝ እንዳትል አልተቀባህም ምን ይውጥሃል አይነት ነው አይ ኤልሳእ ትሁት ሰው አውቄአለሁ ዝም በሉ አላቸው በመቀጠልም እነዚህን የነብያት ልጆች ከመካከላቸው አምሣ ሰዎች ሆነው በፊታቸው ርቀው ቆሙ የመጨረሻውን በዮርዳኖስ ማዶ ያለውን የኤልሳእን ጉድ ሊያዩ ኤልያስ እና ኤልሳእ ዮርዳኖስን ከፍለው ተሻገሩ እነ ኤልሳእ ከዮርዳኖስ ማዶ የነብያት ልጆች ከዮርዳኖስ ወዲህ ጉድ ሊታይ በመጨረሻ ኤልያስ ኤልሳእን ከአንተ ሳልወሰድ የምትፈልገውን ጠይቅ አለው ወገኖቼ በኤልሳእ  እንዴት እደነቃለሁ መሰላችሁ ሁሉን በጽናት ተቋቁሞ መሻቱ ወደሚፈጸም የመጨረሻ ሰዓት ደረሰ አንተም ልትሄድ ነው እኔም ድካሙ ሰልችቶኛል እንደ ጥንቱ ወደ ሥራዬ እመለስ ዘመንድ አሁን ሀብት የለኝም ስለዚህ ብርና ወርቅ ስጠኝ፤ ሀብቴን መልስልኝ አላለውም ይልቅ አንተ የጀመርከውን ሰማያዊ ሥራ በብቃት እወጣው ዘንድ ሁለት እጥፍ መንፈስ አለው፥ ሃሌ ሉያ የገባው ለዓላማው ጽኑ ወደ ኋላ የማያፈገፍግ ብርቱ የሚደንቃችሁ የኤልሳእ ጥያቄ ኤልያስን አስደነገጠው እሳት ከሰማይ ይውረድ ሲል ሰማይ ይዘጋ ይከፈት ሲል በሙሉ ልቡ እንዳልተናገረ እንደምንም ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ አስቸጋሪ ጥያቄ ጠየክ አለው አይገርምም ያንን ታላቅ ነብይ የሚፈትን የልብ መሻት አይ ኤልያስ አልኩ በልቤ እሳት ከሰማይ ሲያወርድ ሰማይ ሲዘጋ ሲከፍት ቅንጣት ያህል ድንጋጤ አልታየበትም የኤልሳእ ጥያቄ ግን እጅግ ፈተነው አስቸጋሪ ጥያቄ አለ ከዚህ በፊት በነበሩ አገልግሎቶች እንዲህ ብሎም አያውቅ ሁሉን በልበ ሙሉነት ያደርግ ነበር ይህ የእምነት ሰው ግን ውስጡን የሚያንቃንቅ ጥያቄ ጠየቀው ወገኖቼ እግዚአብሔር ታማኝ አይደል ኤልያስን በአውሎ ንፋስ ወደ ሰማይ ሲወስደው ለኤልሳእ ግን ሁለት እጥፍ መንፈስ ሰጠው ይህ የዓላማ ሰው የልቡ ደረሰ የውስጥ ረሃቡን አገኘ ከኤልያስ የወደቀውን መጎናጸፊያ አነሣ በዮርዳኖስ ፊት ለፊት ቆመ በመጎናጸፊያውም ውሃውን መታው ተከፈለ ጉዱን ሊያዩ የተሰበሰቡ የነቢያት ልጆች ከፊት ለፊት አንድ አስደንጋጭ ነገር

ይቀጥላል......

በ                                        በሔኖክ ተሾመ



# የግጥም መድብል

## ተናገር ዝም አትበል፤

ንጥቂያው ተፋፍሟል
የጦሩ አውድማ ሁከት በዝቶበታል
የጨለማው ሥራ ያየለ ይመስላል
በቀኝም በግራም ሽዎችን ይነጥቃል፤
ጩኸቱም በርክቷል ካቀበቱ ወዲያ
የድረሱልኝ ድምፅ የሰዎች ጫጫታ
ማን ይሆን ጣልቃ ገብቶ ችግር የሚፈታ
የታመነ ባሪያ የሚኖር ለጌታ፤
እስኪ እናስታውሰው የጥንት የጥንቱን
ያባቶች ተጋድሎ የወንጌልን ክብሩን
በድንጋይ ተወግሮ እስኪፋኖስ ሲሞት
ዮሐንስ ሲቀላ ሲሆን የሰይፍ እራት
ግማሹ በፈላ ዘይት ውስጥ ሲጣሉ
ለአውሬ ተሰጥተው እንክብት ሲበሉ
ያለ እርህራሔ በግፍ ሲገደሉ
ምክንያቱ ምን ነበር የዚህ ነገር ሁሉ
ብለን ብናስተውል ቢፈተሽ ከሥሩ
ስለ ወንጌል ከቶ ምዝ አንልም ቢሉ
አይደል ሰበባቸው እንዲህ ሲሰቃዩ፤
ታድያ የኛ ዘመን ዙሪያ ገባው ሲታይ
ኃጢያት ፅድቅ መስሎ ቆሟል አደባባይ
የሚገልጠው ጠፍቶ እርቃኑን የሚያሳይ
ስንቶች በደጅ ቀሩ ታንቀው በአታላይ....
ሲኦልም ይውጣል አይጠረቃ ሆዱ
እኛ ተዘናግተን ስንቶቹ ነጎዱ፤
ከአደባባይ እንውጣ እስከመቼ ዝምታ
እኛ እውነትን አውቀን ያለመናገር ቸልታ
ከቶ ዝም አንበል እንነሳ እንናገር
እኛ ቁጭ ብለን ሌላ ማን ይመስክር
አዋጅ አዋጅ እያልን ሁሌ እንናገረው

እየሱስ ያድናል የኃጢያት ፈውስ ነው
በሃብታሙ አስረስ(ሃብቴ)

## በሞት ድል መንሳት

ድል መንሣት በሞት
ጀግናው ስም ወጣለት
ሺ ገዳይ ተባለ
በሰቀለው ጩኸት
ሟች ከመሬት ዋለ
ገዳይ ሲወደስ
ሟች ተረሣ ቀረ

ብርቱ አላፍር አለ
ፎከረ ሸለለ
በድል አድራጊ ክብር
ቀናት ተቆጠረ
ቀን ቀንን ወለደ
ደግሞ እንደዚህ ሆነ

ሟች ሥም ወጣለት
ገዳይ ተሸነፈ
ብርታቱ ረገፈ
ሞትም ጥበብ ሆኖ
ሞትን በሞት ሽሮ
የገዳዩን ብርታት ጥሎ አንከባሎ
በድል አድራጊነት መቃብር ፈንቅሎ
ጌታ ኢየሱስ ቆመ ዳግም ሕያው ሆኖ
በአላዛር ሣህሉ

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በቦስተን
ETHIOPIAN EVANGELICAL CHURCH BOSTON
88 TREMONT STREET, BOSTON, MA, 02108
T: 617-523-5058 F: 617-523-5058
www.eecBoston.org